የ ድ ሬ ዳ ዋ   አ ስ ተ ዳ ደ ር

# ድ ሬ  ነ ጋ ሪ ት  ጋ ዜ □

# D I R E  N E G A R I T G A Z E T A

## OF THE DIRE DAWA ADMINISTRATION

| አንደኛ ዓመት ቁጥር 3<br>ድሬዳዋ ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. | በድሬዳዋ አስተዳደር<br>ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 1st Year No. 3<br>DIRE DAWA - 5th August, 2008 |
|---|---|---|

## አዋጅ ቁጥር 3/2000

### <u>የድሬዳዋ አስተዳደር የከተማ ቀበሌ አስተዳደር አካላትን እንደገና ለማቋቋም እና አደረጃጀታቸውንና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ</u>

የቀበሌ አስተዳደሮች የሚያከናውኑት የልማትና የመልካም አስተዳደር ተግባራት ቀልጣፋና ውጠ ,ታማ ለማድረግ እንዲቻል እና አፈፃፀማቸ ውም ቀጣይነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው እንዲሆን መደረግ እንዳለበት በመታመኑ፤

የቀበሌ አስተዳደሮችን አደረጃጀት ከአስተዳደሩ ካቢኔ አደረጃጀት ጋር ተቀራረቢነት ያለው እንዲሆን ማድረግና እንዲሁም ተግባርና ሥልጣናቸ ውን በሕግ መወሰን በማስፈለጉ፤

## PROCLAMATION NO. 3/2008

### <u>A PROCLAMATION ENACTED TO ESTABLISH DIRE DAWA ADMINISTRATION URBAN KEBELE ADMINISTRATIVE BODIES AND REDETERMINE THEIR ORGANISATIONAL STRUCTURE ,</u>

WHERE AS, its believed to make the execution of developmental and good governance activities carried on by the Kebele Administration sustainable, transparent and accountable, in order to make them effective and efficient;

WHERE AS, it is necessary to harmonies the organizational structure of the Kebele Administration with that of the cabinet of the administration and to determine their power and duty by law;

የድሬዳዋ አስተዳደር ምክር ቤት በድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 አንቀጽ 12/1/ /ሀ/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን አዋጅ አውጥቷል።

NOW, THERE FORE, in accordance with the power given to it under Article 12(1)(a) of the Dire Dawa Administration Charter proclamation No. 416/1996 , the Dire Dawa Administration council has proclaimed the following.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

## PART ONE

## GENERAL

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ «የድሬዳዋ አስተዳደር የከተማ ቀበሌ አስተዳደሮችን እንደገና ለማቋቋም እና አደረጃጀታቸውንና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 3/2000» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as "Proclamation enacted to re-establish the Dire Dawa Administration Urban Kebele Administrative bodies and re-determine their organizational structure, as well as their power and function proclamation No. 3/2008.

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. «ቻርተር» ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 416/1996 ነው።
2. «አስተዳደር» ማለት የድሬዳዋ አስተዳደር ነው።
3. «የከተማ ቀበሌ» ማለት የአስተዳደሩ ሁለተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው።
4. «ምክር ቤት » ማለት በቻርተሩ አንቀጽ 10/3/ /ሀ/ መሠረት የተቋቋመ የከተማ ቀበሌ ምክር ቤት ነው።
5. «ቋሚ ኮሚቴ» ማለት የምክር ቤቱንና የካቢኔውን የሥራ ተግባር ለማቀላጠፍ ሲባል በምክር ቤቱ የሚቋቋም አካል ነው።

**2. Definition**

In this proclamation, unless the context requires otherwise:

1. "Charter" means the Dire Dawa Administration Charter proclamation No. 416/2004.
2. "Administration" means the Dire Dawa Administration.
3. "Urban Kebele" means the second administrative level in the hierarchy of the administration.
4. "Council" means an Urban Kebele council which is established as per article 10 (3) (a) of the charter.
5. "Standing Committee" means a body established by the council with

a view to expedite the activities of the council and the cabinet.

3. **መቋቋም**

1. ዝርዝራቸው ከዚህ አዋጅ ጋር በአባሪነት የተመለከተው 9 የከተማ ቀበሌ አስተዳደሮች ሕጋዊ ሰውነት አግኝተው ተቋቁመዋል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ቢኖርም የቀበሌ አስተዳደሮች ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ ሊቀንስ ወይም ሊጨምር ይችላል፡፡
3. የቀበሌዎች አስተዳደር አከላለልና ወሰን በአስተዳደሩ ምክር ቤት ይወሰናል፡፡

## ክፍር ሁለት

## ስለ ቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀትና የቀበሌ ምክር ቤት

4. **የቀበሌ አስተዳደር አደረጃጀት**

የቀበሌው አስተዳደር አደረጃጀት እንደሚከተለው ነው፡፡

1. የቀበሌው ምክር ቤት፣
2. አፈ-ጉባኤ፣
3. ፀሐፊ፣
4. ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣
5. ቋሚ ኮሚቴ፣
6. ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣
7. ሥራ አስኪያጅ፣
8. ማህበራዊ ፍርድ ቤት፣
9. ሌሎች አስፈፃሚ አካላት፡፡

5. **ስለ ቀበሌው ምክር ቤት አባላትና ተጠሪነት**

1. የቀበሌው ምክር ቤት የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው፡፡

3. **Establishment**

1. Nine urban Kebele Administration, the details of which is providing in the annex to this proclamation, and hereby established having a legal personality.
2. Notwithstanding the provision of sub-art(1) of this article, the number of the Kebele administration may increase or decrease, as is necessary,
3. The demarcation and the boarder of the kebele administration shall be determined by the council of the administration.

## PART TWO

## The Organizational Structure of The Kebele Administration And The Kebele Council

4. **The Organizational Structure of the Kebele Administration**

The organizational structure of the Kebele council shall include the following.

1. The kebele Council,
2. The Spokes Person,
3. The Secretary,
4. The Chief Executive,
5. The Standing Committees,
6. The Deputy Chief Executive,
7. The Manager,
8. The Social Court and
9. Other executive bodies.

5. **<u>Members of Kebele council and their accountiablility.</u>**

1. The Kebele Council shall be the highest authoritative body for the Kebele residents.
2. የምክር ቤቱ አባላት በየአምስት ዓመቱ በቀጥታ በቀበሌው ነዋሪ ይመረጣሉ::
3. የምክር ቤቱ አባላት ተጠሪነታቸው ለምክር ቤቱና ለመረጣቸው ነው::

6. **<u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>**

1. የአስተዳደሩ ምክር ቤት እና ካቢኔው በየጊዜው የሚያወጣቸው ሕጎች ፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ዕቅዶች በቀበሌው ውስጥ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፣
2. የአስተዳደሩ ምክር ቤት ከሚያወጣቸው ፖሊሲዎች፣ ሕጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር በማይቃረን መልኩ የአካባቢ ማህበራዊ ጉዳይ መመሪያ አውጥቶ በሥራ ላይ ያውላል::
3. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የምክር ቤቱን አፈ-ጉባኤ፣ ፀሐፊ እና የቀበሌውን ዋና ሥራ አስፈፃሚ በምርጫ ይሰይማል፣ የቀበሌው አስተዳደር ካቢኔ ያደራጃል::
4. የነዋሪውን ሕዝብ ትችትና አስተያየት መሠረት በማድረግ በቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ተመርጠው የሚቀርቡለትን የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ይሾማል::
5. የምክር ቤቱን ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፣ የሥራ ክፍፍልና ምደባ ይወስናል::
6. ለቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ የሚጠቅሙ ዕቅዶችን ያወጣል ተግባራዊነታቸውንም በቅርበት ይከታተላል::
7. በቀበሌው ዕቅድ ላይ በመወሰን እና የበጀት ድልደላ በማድረግ ለአስተዳደሩ ምክር ቤት ያቀርባል::

2. Members of the Council shall be elected directly by the residents of the kebele every five years.
3. The members of the council shall be accountable to the council and to the people who elected them.

6. **<u>Power and Function of the Council</u>**

1. It shall implement the laws, regulations, directives and plans issued by the administrative council and the cabinet, with in the Kebele,
2. In a manner which is not contrary to the policies, rules, regulation and directives issued by the administrative council, implements a regulation it issued on matters of local social affairs.
3. It shall nominate by election, the speaker of the council, secretary and the chief executive of the Kebele, from among the members of the council; organize cabinet of the Kebele administration.
4. It shall appoint the Judges of the social court, elected and presented to it by the Kebele chief executive based on the critics and opinion of the society.
5. It shall establish different committees of the council; determine a work division and assignment.
6. It shall propose plans that benefit to the residents of the Kebele and follow up their implementation closely.

7. Based on the plan of the Kebele, it shall allocate the budget and present it to the administrative council accordingly.

8. የቀበሌው አስተዳደር በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል::
9. የቀበሌውን ነዋሪ ሕዝብ ለልማት ሥራ ያነሳሳል፣ የተፈጥሮ ሀብትን ልማትና እንክብካቤ ሥራ በቅርበት ይከታተላል::
10. የቀበሌው ነዋሪ ሕዝብ ሰላምና ደህንነት መጠበቁንና ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል::
11. ስለ አሰራሩ የሚወሰን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል::

## 7. <u>ስለ ምክር ቤቱ አመራር</u>

ምክር ቤቱ የራሱ ጽ/ቤት የሚኖረው ሆኖ ከአባላቱ መካከል በሚመረጡ እንደ አፈ-ጉባኤ እና እንደ ፀሐፊ ይመራል::

## 8. <u>ስለ ምክር ቤቱ አሠራርና የአባላት ሥነምግባር</u>

የምክር ቤቱ አሠራርና የአባላት ሥነ-ምግባር በምክር ቤቱ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል::

## 9. <u>የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ</u>

አፈጉ-ባኤው ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤቱ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤

1. የሥራ ዘመኑ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፣ ሥራውን በፈቃዱ ሲለቅ ወይም በምክር ቤቱ ከኃላፊነቱ ሲታገድ ወይም የምክር ቤት አባልነቱ ሲቋረጥ ከኃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፤ ዝርዝሩ በቀበሌው ምክር ቤት በሚወጣ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፤
2. የምክር ቤቱን ጽህፈት ቤት ይመራል፣

8. It shall ascertain the proper implementation of budget of the Kebele Administration.
9. It shall initiate the residents of the Kebele for developmental works and follows up the protection of natural resource development closely.
10. It shall ensure the protection of peace and security of the residents and ensure Law and order is respected.
11. It shall issue a code regulating its operation.

## 7. <u>Heads of the Council</u>

The council shall have its own office, which is headed by one spokes person and one secretary; elected among the members of the council.

## 8. <u>Rules of Operation of the council and members code of conduct</u>

The operation of the council and member's code of conduct shall be determined by regulation here by, enacted by the council.

## 9. <u>Spokes person of the Council</u>

Being accountable to the kebele council, the spokesperson shall have the following powers and functions:

1. The term of the office of the spokes person shall be the term of the council. Where he resigns, suspended from the post by the council or his membership of the council is terminated, he may be dismissed from his authority. The detail shall be determined by the

regulation enacted by the kebele council.

2. He shall direct the office of the council.

3. ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግን ኙነት ምክር ቤቱን ይወክላል፣
4. የምክር ቤቱን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመ ራል፣ የምክር ቤቱን ኮሚቴዎች ያስተባ ብራል፣
5. የምር ቤቱን ጽህፈት ቤት በጀት ያዘጋ ጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

10. **<u>የምክር ቤቱ ፀሐፊ</u>**

1. ፀሐፊው ተጠሪነቱ ለአፈ-ጉባኤው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖ ሩታል፣
   ሀ. ከአፈ-ጉባኤው ጋር በመመካከር የምክር ቤቱን አጀንዳ ያዘጋጃል፣ የምክር ቤቱን ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፣
   ለ. የምክር ቤቱና የምክር ቤቱ ኮሚ ቴዎች ቃለ-ጉባኤዎችና ሰነዶች እንዲያዙና እንዲጠበቁ ያደርጋል፣ ቃለ ጉባኤዎችን ያሰራጫል፣
   ሐ. በአፈ-ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡
2. ሥራውን በራሱ ፈቃድ ሲለቅ፣ በምክር ቤቱ ከኃላፊነቱ ሲታገድ ወይም የምክር ቤቱ አባልነቱን ሲያ ቋርጥ ከኃላፊነቱ ሊሰናበት ይችላል፣
3. የሥራ ዘመኑ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

11. **<u>የምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜ እና የሥራ ዘመን</u>**

1. የቀበሌ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባውን በሦስት ወር አንድ ጊዜ ያካሂዳል፣

3. He shall represent the council in any relation, made with third parties.
4. He shall call the council for meeting, direct the meeting and coordinate the committee of the council,
5. It shall prepare the budget of the office of the council and implements the same on approval.

**10. <u>Secretary of the council</u>**

1. Being accountable to the spokes person, the secretary of the council shall have the following power and function.
   a. In discussion with the spokes person, he shall prepare the agenda of the council; take the minutes of the council as well,
   b. He shall take and hold the minutes and documents of the council and the committee, kept and protected and distribute the minutes as well,
   c. He shall execute other activities assigned to him by the spokes person.
2. Where he resigns, suspended by the council or where he terminates his membership, he may be dismissed of his authority.
3. His term shall be the term of the council.

**11. <u>Time of Assembly and term of the Council</u>**

1. The kebele council shall have its ordinary meeting once with in three months of period.

2. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከሁለት ሦስተኛ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡ የምክር ቤቱ ውሣኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት የምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል፡፡
3. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ የሥራ ዘመኑ ከማብ ቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፡፡ የቀድሞው ምክር ቤት የሥራ ዘመን በተጠናቀቀ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ አዲሱ ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፡፡
4. የቀበሌ ምክር ቤት ስብሰባ በግልጽ ይካሄዳል፡፡

ምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በማያደር ግበት ወቅት አፈ-ጉባኤው አስቸኳይ ስብ ሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡ የቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አስቸ ኳይ ስብሰባ እንዲካሄድ ከጠየቁ አፈ-ጉባ ኤው የምክር ቤቱን ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡

12. <u>የቀበሌ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አስያየምና የሥራ ዘመን</u>

1. የቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በምክር ቤቱ ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ባገኘው የፖለቲካ ድርጅት አቅራቢነት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል ተመርጦ ይሰየማል፡፡
2. በሕግ ካልተወሰነ በስተቀር የቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሥራ ዘመን የቀበ ሌው ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆ ናል፡፡

2. There shall be a quorum where two third majority of the members of the council are found in a meeting; the decision of the council shall be passed by the majority vote of the members found in the meeting.

3. The council shall have the term of five years. There shall be an election one month before the expiry of the term of the council. The new council shall commence its operation with in 15 days after the end term of the ex-council.

4. The meeting of the council shall be held in public. The speaker of the council may call for an extra-ordinary meeting during the time at which the council is not at a regular meeting. The speaker of the council is duty bound to call an extra- ordinary meeting where he is so requested by more than half members of the council or by the chief executive of the kebele.

**12. <u>Nomination and terms of the office of the Kebele chief executive.</u>**

1. The chief executive of the Kebele shall be nominated among the members of the council, up on the recommendation of the party with a majority seat.

2. Unless the contrary is provided by law, the term of the Kebele chief executive shall be of that of the kebele council.

13. <u>የቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ተጠሪነቱ ለቀበሌው ምክር ቤት እና ለአስተዳደሩ ከንቲባ ሆኖ ቀበሌውን ይመራል፣
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠ ቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ስራ አስፈፃሚው፤
   ሀ. የቋሚ ኮሚቴ አባላትን፣ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ ሥራ አስኪ ያጅ እና የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞችን ለቀበሌው ምክር ቤት በማቅረብ ሹመታቸ ውን ያፀድቃል::
   ለ. የቀበሌው ዓመታዊ ዕቅድና የበጀት ድልድል ሀሣብ በቀበሌው ቋሚ ኮሚቴ ከመከረበት በኋላ ለቀበ ሌው ምክር ቤት ያቀርባል::
   ሐ. የቀበሌውን ቋሚ ኮሚቴ ይሰበስባል::
   መ. በቀበሌው ሕግና ሥርዓት ያስከ ብራል፣ ከቀበሌው አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ ችግር ሲያጋጥም ለአስተዳደሩ ከንቲባ ያሳውቃል::
   ሠ. ከቀበሌው ሥራ አስኪያጅ የሚቀ ርብለትን ሪፖርት ይቀበላል፣ መር ምሮ ውሣኔ ይሰጣል::
   ረ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት በቀበሌው ቋሚ ኮሚቴ እንዲገመገም ያደርጋ ል፣ ውጤቱን ለቀበሌው ምክር ቤት እና ለአስተዳደሩ ዋና ሥራ አስ ፈፃሚ ሪፖርት ያደርጋል::
   ሰ. በብሔራዊና በሕዝብ በዓላት ሥነ-ሥርዓቶች ላይ እንደ አስፈላጊነቱ ቀበሌውን ይወክላል::

13. **<u>Power and function of the Kebele Chief Executive.</u>**

1. Being accountable to the Kebele council and the Mayor of the administration, he shall direct the Kebele.
2. Without prejudice to the general provision of sub-article (1) of this article, the chief executive:-
   a. Shall recommend members of the standing committees, the deputy chief executive and the judges of the Kebele social courts for approval to the Kebele Council.
   b. After dealing with the Kebele standing committee about the Kebele's annual action plan and budget allocation, shall submit it to the Kebele council.
   c. He shall assemble the standing committees of the Kebele.
   d. He shall enforce law and order in the Kebele; When the Kebele faces a security problem beyond its capacity, shall notify the same to the mayor of the administration.
   e. He shall receive the report submitted to him by the kebele manager; scrutinize and give decision on it.
   f. He shall made the municipal services get evaluated by the Kebele standing committees, and report the finding to the Kebele council and the chief executive of the administration.

g. Whenever, it is necessary, he may represent the Kebele on national and public holydays.

ሸ. ዓመታዊና ወቅታዊ ሪፖርት ለአስ ተዳደሩ ከንቲባና ለቀበሌው ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

ቀ. የአካባቢ ልማት ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን በበላይነት ይመራል፡፡

በ. በቀበሌው ምክር ቤት እና ከአስ ተዳደሩ ዋና ስራ አስፈፃሚ የሚሰ ጡትን ሌሎች ተግባራት ያከና ውናል፡፡

14. <u>የቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ</u>

1. ተጠሪነቱ ለቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃ ሚና በጋራ ለሚወሰነው ውሣኔም ለቀበ ሌው ምክር ቤት የሆነ የሚከተሉት አስፈፃሚ አካላት ያሉት ቋሚ ኮሚቴ ተቋቁሟል፡፡

ሀ. የአቅም ግንባታ እና ትምህርት ቋሚ ኮሚቴ ፣

ለ. ጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ ተቋማት ልማት ቋሚ ኮሚቴ፣

ሐ. የአካባቢ ፀጥታ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ፣

መ. የጤናና ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ፣

ሠ. የማስታወቂያ ሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመ ለከተው ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉት ሥል ጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

ሀ. በቀበሌው ዕቅድና የበጀት ድልድል ሀሣብ ላይ ይመክራል፣

ለ. በቀበሌው ውስጥ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና የከተማ የበላይ አካላት ውሣኔዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡

h. He shall submit an annual and periodic report to the Mayor of the administration and the Kebele Council.

i. Being served as a chairperson of the environmental development committee and directs the same.

j. He shall carry out other activities assigned to him by the council and chief executive of the administration.

**14. <u>Standing Committees of the Kebele</u>**

1. A standing committees, which is accountable to the chief executive of the Kebele and to the Kebele council for its collective decision, involving the following executive bodies are here by established,
   a. Capacity building and Education Standing Comm- ittee,
   b. Micro and Small business enterprise standing comm- ittee,
   c. Local Security Affair Stand- ing Committee,
   d. Health and Social Affairs Standing Committee,
   e. Information and Public Rela- tion standing committee.
2. The standing committees provided in sub-article (1) of this article shall have the following power and function.

a. Shall discus on the proposed budget allocation and action plan of the Kebele,
b. It shall ensure the implementation of policies, laws, regulation and decisions of higher organs of the town.

ሐ. በቀበሌው ምክር ቤትና በዋና ሥራ አስፈፃሚው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

15.**<u>የቀበሌ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሥል ጣንና ተግባር</u>**

የቀበሌው ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ተጠ ሪነቱ ለዋናው ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ፣

1. የቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ በሌለበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይች ልበት ጊዜ እርሱን ተክቶ ይሰራል::
2. ለጤናና ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ የተሰጠውን ተግባር በኃላፊነት ይመ ራል፤
3. በቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚሰጡ ትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

16. **<u>የቀበሌው ሥራ አስኪያጅ ሥልጣንና ተግባር</u>**

የቀበሌው ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::

1. የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቀበ ሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ የቀበ ሌው የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶች አስፈፃሚ በመሆን ይሰራል::
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠ ቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የቀበ ሌው ሥራ አስኪያጅ፣

ሀ. በቀበሌው የማዘጋጃ ቤት አገል ግሎት አሰጣጥ የተቀላጠፈ፣ውጤ ታማና ፍትሀዊ እንዲሆን ሀሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል::

c. They shall implement other activities entrusted to them by the Kebele council and by the chief executive.

15. **<u>Power and function of deputy chief executive of the kebele council</u>**

Being accountable to the chief executive of the Kebele, the deputy chief executive:-

1. May represent the chief executive in his absence or when he is not able to work.
2. shall run the activates entrusted to the social affairs standing committee and acts as its head,
3. Shall carry out other activities assigned to him by the Kebele chief executive.

16. **<u>Power and Function of the Kebele Manager</u>**

The Kebele manager shall have the following powers and functions.

1. Being accountable to the Kebele chief executive, the Kebele manager shall work as executive of the Kebele municipal services.

2. Without prejudice to the general provision of the sub-article (1) of this article, the manager of the Kebele shall have the following powers and functions to:-

a. Forward proposal that make the municipal service delivery

efficient, effective and fair; implement the same upon approval.

ለ. ሠራተኞችን በድሬዳዋ አስተዳደር መንግስት ሠራተኞች አስተዳደር ሕግ መሠረት ያስተዳድራል፡፡

ሐ. ከቀበሌው የማዘጋጃ ቤት አገል ግሎት ሰጪ አካላት ኃላፊዎች የተ ውጣጣና በከተማው ሥራ አስኪ ያጅ በሚወሰነው መሠረት የሚሰራ የሥራ አመራር ኮሚቴ ያቋቁ ማል፣ ይመራል፡፡

መ. የማዘጋጃ ቤት አገልግሎትን የሚ መለከቱ ፖሊሲዎች ሕጎችና ውሣኔ ዎች ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ሠ. ስለሥራው አፈፃፀም ለከተማው ሥራ አስኪያጅና ለቀበሌው ዋና ስራ አስፈፃሚ ወቅታዊና ዓመ ታዊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

ረ. ከከተማው ሥራ አስኪያጅ እና ከቀ በሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ የሚ ሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከና ውናል፡፡

በ. የቀበሌው ሥራ አስኪያጅ በቀበሌ ካቢኔ ሰብሳባዎች ላይ ያለድ ምጽ መሳተፍ ይችላል፡፡

17. <u>የቀበሌ አስተዳደር ካቢኔ አባላት</u>

የቀበሌ አስተዳደር ካቢኔ አባላት የሚከ ተሉት የሆናሉ፡፡

1. የቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ፣
2. የቀበሌው ምክትል ዋና ሥራ አስ ፈፃሚ፣
3. በአንቀጽ 14 /1/ ላይ የተጠቀሱት ቋሚ ኮሚቴ ኃላፊዎች፣
4. ዋና ሥራ አስፈፃሚው በአባልነት እን ዲሳተፉ የሚመርጣቸው የቀበሌው አስ ተዳደር ሌሎች ኃላፊዎች፡፡

b. Administer employees in accordance with the Dire Dawa Administration civil servants proclamation.
c. Establish and direct the management committee constituted by the heads of Kebele municipal service rendering bodies which functions in accordance with the decision of the manager of the city.
d. Implement policies, laws, and decisions concerning municipal services.
e. Submit annual and periodic performance reports to the manager of the city and chief executive of the Kebele.
f. Carryout other functions assigned to him by the city manager and chief executive of the kebele.
g. The manager of the Kebele may participate in the meetings of the Kebele cabinet without vote.

**17. <u>Members of Kebele Administration Cabinet.</u>**

The members of the Kebele administration cabinet shall be the following.

1. The chief executive of the kebele,
2. The deputy chief executive of the Kebele,

3. The heads of the standing committees referred to under article 14(1) of this proclamation,
4. Other heads of administration of the Kebele as are appointed to involve participate as a member thereof by the chief executive of the kebele.

## ክፍል ሦስት

## ስለ ቀበሌ አስተዳደር ካቢኔ

18.**ስለ ቀበሌ አስተዳደር ካቢኔ አባላት ተጠሪነት**

የቀበሌ አስተዳደር ካቢኔ ተጠሪነቱ ለቀበሌው ዋና ሥራ አስፈፃሚ እና ለመረጠው የቀበሌ ምክር ቤት ነው::

19. **የቀበሌው አስተዳደር ካቢኔ ሥልጣንና ተግባር**

1. የቀበሌ አስተዳደር ካቢኔ አባላት በግልና በወል የቀበሌውን አስተዳደር ሥራ ይመ ራሉ፣ ያስተባብራሉ::
2. የካቢኔ አባላት በጋራ ሥልጣናቸው ለሚያ ሳልፉት ውሳኔና ለሚፈጽሙት ተግባር የጋራ ኃላፊነት አለባቸው::
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ የቀበሌ አስተዳደር ካቢኔ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል::
   ሀ. ቀበሌ የልማትና የነዋሪው ቀጥተኛ ተሳትፎ ማዕከል በመሆኑና በቀበሌ ደረጃ ሊሰጡ ለሚችሉ አገልግሎ ቶች ጣቢያ ሆኖ የቀበሌውን ነዋሪ ዎች፣ መንግስታዊና መንግ ስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለልማት ያነሳ ሳል::
   ለ. የአካባቢው ልማት ሥራዎች የከተ ማው ፕላን፣ የግንባታ ሕጎችና ደረጃ ዎች ጠብቀው እንዲሰሩ ድጋፍ ያደ ርጋል፣ ሕገወጥ ግንባታንም ይቆጣጠ ራል::

## PART THREE

## KEBELE ADMINISTRATION CABINETS

**18.Accountability of the Kebele Administration Cabinets.**

The Kebele administration cabinets shall be accountable to the chief executive of the kebele and to the council of the Kebele which elected them.

**19.The power and function of the Kebele Administration Cabinet.**

1. The members of the kebele administration cabinet shall coordinate and direct the administrative activities of the Kebele severally and jointly.
2. The members of the cabinet shall have collective responsibility for the decisions they rendered and for the activities they perform in their common authority.
3. Without prejudice to sub-articles (1) and (2) of this provision, the members of the Kebele administration cabinet shall have the following powers and functions individually.
   a. Being kebele is a center for development and direct participation of the residents, it shall inspire for development to the kebele dwellers, governmental and non governmental organizations and investors for those services that can be provided at kebele level.

b. Provide a support and super- vise the accomplishment of local developmental active- ates in accordance with the city plan, construction laws and standards; control illegal constructions.

ሐ. በቀበሌው የሥነሥርዓት አስከባሪዎ ችን ያሰማራል፣ የሚያከናውኑትን ስራ ይቆጣጠራል፣ በቀበሌው ክልል ውስጥ ሕገወጥ ድርጊቶች እንዳይ ካሄዱ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

መ. የቀበሌው ነዋሪ ሕብረተሰብ የአካባ ቢውን ጽዳት እንዲጠበቅና አካባቢ ውን እንዲያስውብ ያስተባብራል ፣ የተሰሩትም እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

ሠ. የቀበሌውን ነዋሪዎች ተሳትፎ ለማጎ ልበት እንዲረዳ የተለያዩ ብዙሀን ማህበራትና ማህበራዊ ተቋማት እን ዲደራጁ ድጋፍ ይሰጣል፣ ያስተ ባብራል፡፡

ረ. በአነስተኛ ጥቃቅን ንግድ ሥራዎችና በዕደጥበብ የተሰማሩ የህብረተሰቡ ክፍሎችን በማህበር እንዲደራጁ ያበረታታል፣ ተገቢውን ድጋፍ የሚ ያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

ሰ. ጎጅ ባህሎችን ለማስወገድ፣ ኤች አይ ቪ/ኤድስን ለመከላከል፣ የበሽታ መከላከልና የመሠረተ ጤና ትምህር ትንና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን በተ መለከተ ለነዋሪው ሕብረተሰብ የት ምህርትና ቅስቀሳ ተግባራት እንዲ ደረግ ያመቻቻል፣ ይከታተላል፣ የጠ ጋና ኬላዎችን ያስተዳድራል፡፡

ሸ. በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ አፀደ ህፃና ትን እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህ ርት ቤቶችን ይከታተላል፣ የመሠ ረተ ትምህርት እንዲስፋፉ ያደር ጋል፡፡

c. Deploy code enforcement personnel in the Kebel and supervise their activities, follow and supervise not to carry out illegal acts with in the Keblele.

d. Coordinate the residents of the Kebele to keep the sanitation of the environment and beautify the same; preserve the already performed activities.

e. Provide support for the establishment of civic associations and social institutions in order to enhance the participation of the kebele residents.

f. encourage the organization of parts of the community enga- ged in small and micro trade activities and handcrafts ship to form associations; facilitate a situation in which they obtain the appropriate sup- port.

g. Shall facilitate for the provision of educational and awareness creation activities to the residents to combat harmful traditional practices, prevent and control HIV/ AIDS, preventions of diseases, basic health education and on other related matters; shall render an assistance to institutions working on prevention and controlling HIV/AIDS in the Kebele .

h. Follow up kindergartens and primary schools that are situated with in the kebele; undertakes expansion of basic education.

ቀ. ከአስተዳደሩ የሚመደብለትን የበጀት ድጎማ መሠረት በማድረግ የቀበሌውን በጀት ይደለድላል ዕቅ ዱን በማጽደቅ ለአስተዳደሩ ያቀር ባል። የደረጃ «ሐ» ግብር ከፋዮችን ግብር ይወስናል፣ ይሰበስባል፣ በአስ ተዳደሩ በሚወጣ ሕግ መሠረት የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት ክፍያዎች ይሰበ ስባል።

በ. በቀበሌው ክልል ስለሚገኙ ክፍት ቦታዎችና የመሬት ይዞታ ሁኔታ የተሟላ መረጃ ይይዛል፣ በአስተ ዳደሩ ባለቤትነት ስር ያሉ ቤቶችም በአስተዳደሩ በሚወጣ ሕግ መሠረት ያስተዳድራል።

ተ. የመናፈሻዎችና የመዝናኛ ቦታዎችን ይንከባከባል፣ ይጠብቃል።

ቸ. ስለቀበሌው ነዋሪዎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን በማጠና ቀር ይይዛል፣ ሲጠየቅም ለሚመለከተው አካል ያስተላልፋል።

20. <u>የቀበሌ አስፈፃሚ አካላት</u>

1. በእያንዳንዱ ቀበሌ ለቀበሌ ቋሚ ኮሚቴ ተጠሪ የሚሆኑ ዴስኮች ይኖራሉ፤ ዝር ዝሩ የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያወጣው ሕግ ይወናል።

2. የቀበሌ ዴስኮች ከሚያስተባብሯቸው አስ ፈፃሚ አካላት ጋር ድጋፍ ሰጪ አገል ግሎቶችን በጋራ ይጠቀማሉ። ዝርዝሩ የአስተዳደሩ ካቢኔ በሚያፀድቃቸው መዋቅራዊ አደረጃጀት መሠረት በሚ ወጣ መመሪያ ይወሰናል።

i. Based on the budget subsidy allotted to it by the administration, allocates the budget of the Kebele, submits the ratified planned budget of the Kebele, Levi tax on schedule "c" tax payers, collects the same, collect municipal services tax in accordance with a directive to be issued by the administration.

j. Keep full information about unoccupied vacant places and the state of land holdings with in the limit of the Kebele; administer houses that are owned by the administration in accordance with a directive to be issued by the administration.

k. Preserve and protect parks and recreational places.

l. Keep and consolidate the socio-economic information's regarding the residents of the Kebele; forwards the same to the concerned organ on request.

## 20. <u>Executive bodies of Kebele</u>

1. There shall be, in each Kebele, desks which are accountable to the Kebele standing committee. The detail shall be determined in a directive issued by the cabinet of the administration.
2. The Kebele desks shall, together with the executive bodies they coordinate, make use of support rendering services. The detail there of shall be determined by the directive issued in accordance with the organizational structure

approved by the cabinet of the administration.

21. ** የቀበሌ የማዘጋጀት ቤት አገልግሎት አካላት ስለ ማቋቋም**

ለቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ የሆኑ የማዘ ጋጅ ቤት አገልግሎት አካላት ይኖራሉ:: ዝርዝሩ በአስተዳደሩ ካቢኔ በሚወጣ መመ ሪያ መሠረት ይወሰናል::

22. **ስለ ቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት**

የቀበሌ አስተዳደር የራሱ ጽህፈት ቤት ይኖ ረዋል:: ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል::

23. **የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት**

የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በቻርተሩ አንቀጽ 31/2/ መሠረት የአስተዳደሩ አንዱ የዳኝነት አካል ሲሆን የድሬዳዋ አስተዳደር የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶችን ለማጠ ናከርና ሥልጣንና ተግባራቸውን እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 2/2000 የተቋቋመ ነው::

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

24 **የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች**

1. በድሬዳዋ አስተዳደር የቀበሌዎች አስተዳደር ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1/1996 በዚህ አዋጅ ተሽሯል::
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉ ትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃ ሚነት አይኖረውም::

21. **Establishment of Kebele Municipal Service Bodies.**

There shall be municipal service bodies which are accountable to the managers of the kebele. The detail shall be provided in the directive to be issued by the cabinet of the administration.

22. **Kebele Administration Office**

The Keble administration shall have its own office. The detail shall be provided by law.

23. **Keble Social courts**

The Keble social court, being one judicial organ of the administration pursuant to article 31(2) of the charter, is established by the proclamation enacted to consolidate and re-determine the power and function of Dire Dawa Administration social courts, proclamation No. 2/2008.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

24. **Repealed and Inapplicable laws**

1. Dire Dawa Administration kebele establishment proclamation No. 1/2004 is hereby repealed.
2. Any proclamation, regulation, directive and customary practice, in

so far as it is inconsistent with this proclamation shall not have applicability in respect of matters provided for in this proclamation.

25. <u>ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

የድሬዳዋ አስተዳደር ካቢኔ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብና መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

26. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ድሬዳዋ ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም.

አደም ፋራህ

የድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ

**25. <u>Power to issue regulation and Directives</u>**

The Dire Dawa Administration cabinet, in so far as it is necessary for the implementation of this proclamation, may issue regulation and directives.

**26. <u>Effective Date</u>**

This proclamation shall enter in to force as of 5th of August 2008.

**Done at Dire Dawa**
**This day of 5th of August 2008**

**ADEM FARAH**

**MAYOR THE DIRE DAWA**

**ADMINSTRATION**